**Institute of Development & Education for Africa, Inc.**

**1199 Whitney Ave Suite 523 Hamden, Ct 06517 Tel: 203-789-1990 or 203-747-2763**
**webmaster@africanidea.org**

**January 4 2019** ነሐሴ ፳፮ ፪ሺ፩፩

# እንረስ ካላችሁ ተስማምተን እንረስ፤ አይሆንም ካላችሁ ተዉት ዳዋ ይልበስ
## We Must Live Together as Brothers or Perish Together as Fools (MLK)

**ገላውዴዎስ ኣርኣያ ዶ/ር** **Ghelawdewos Araia, PhD**

ለዚሁ መጣጥፍ አርእስት ይሆን ዘንድ የተጠቀምኩበት በእውቀቱ ስዩም ከደረሰው **ከአሜን ባሻገር** ከሚል መጽሐፍ የተዋስኩት ነው። ርእሰ ነገሩን በይበልጥ ለማጠንከር ደግሞ “We must live together as brothers or perish together as fools” የሚለውን የማርቲን ሉተር ኪንግ ብልህ ጥቅስ አክሌበታለሁ። ሁለቱ የሚደጋገፉ ሐሳቦች ሆነው አሁን በኢትዮጵያ የተከሰተውን አስፈሪና አሳሳቢ ቀውስ መፍትሄ ይገኝለት ዘንድ በመጠኑም ቢሆን ለሰላም፡ ለእርጋታና፡ ለብልጽግና አስተዋጽኦ ለማድረግም ጭምር ነው።

ለበርካታ ዓመታት ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ስጽፍ፡ ስተርክ፡ ሳገናዝብና፡ ስዘግብ ቆይቻለሁ። ነገር ግን እኔ ወይም ሌሎች አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን እንደፈለግነውና እንደተመነኘው ባገር ፍቅር የተመሠረተ ውህደት ሳይሆን፡ አገራችን ኢትዮጵያ የምትበጠብጥበት ሁኔታ ነው የተፈጠረው፤ ይህ አስፈሪና አሳሳቢ ክስተት ግን ዝም ብሎ ባንዳፍታ ከፊታችን የተደቀነ ሳይሆን ለዓመታት ሲቆለል ቆይቶ አሁን እንደ እሳተ ጎመራ የፈነዳ ጉዳይ ነው። እኔ በበኩሌ የመበጣበጡና የመበጣጠሱ ነገር ቀደም ብዬ አይቼው ነበር፤ የዛሬ ፳፬ ዓመት Ethiopia: The Political Economy of Transition በተሰኘው መጽሐፌ ውስጥ “የብሔርና ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት በክልል መስተዳድሮች መተግበሩ መልካም ሆኖ፡ ክልሎቹን በቋንቋ እና ጎሳ መወሰናቸው ግን የኋላ ኋላ የብሔር ንቃተ ኅሊና ጎልምሶ ኢትዮጵያዊ የሚለውን የጋራ ማንነት ይሸረሽርና ኢትዮጵያውያን ባልገመቱትና ባልጠበቁት ውጥንቅጥ ውስጥ ሊዘፈቁ ይችላሉ” ብዬ ነበር። ያው ያልኩትን ነገር ተከሰተ፤ አብዝሃ ሕዝቡ በጎጥና በክልል ታጠረ፤ የኢትዮጵያ አንድነት ደግሞ ተፍረከረከ።

ኢትዮጵያ በብዙ ረገድ ከሌሎች አገሮች የተለየች ብትሆንም ቅሉ ከሁሉም በላይ ግን አይደለችም። እርግጥ ነው በአፍሪቃ ነፃነቷን ጠብቃ የቆየች ብቸኛ ሃገር ናት (ዕድሜ ለአርብኞቹ ቅድመ አያቶቻችን)፤ የሰው ዘር መገኛ ናት፤ የግሪኩ ፈላስፋ ሆመር (800 ከክርስቶስ በፊት) ኢትዮጵያን “መላእክት የሚያርፉባት አገር ናት” ይላታል፤ ሌላው የግሪክ ተራኪ ዲዮዶሮስ ሲስለስ (90-30 ከክርስቶስ በፊት) የተባለ ደግሞ “ኢትዮጵያን ለማጥቃት የሚቃጡና የሚነሱ ኃይሎች ብዙ ናቸው፤ ከነሱ ግን አንድ እንኳን የሚሳካለት አይኖርም” ይላል። በትላልቅ የኃይማኖት ቅዱሳን መፃሕፍት ከማንኛውም አገር በይበልጥ የምትጠራ ኢትዮጵያ ናት፤ እአአ በአስራሰባተኛው ክፍለዘመን የአትላንቲክ ውቅያኖስ የኢትዮጵያ ውቅያኖስ ተብሎ ይጠራ ነበር፤ አሁን ባለንበት ዘመን ደግሞ ኢትዮጵያ የአፍሪቃ መናኸርያ ሆናለች፡ አዲስ አበባ ደግሞ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፤ የአፍሪቃ መዲና ከመሆኗ ባሻገር የዓለም ዲፕሎማሲና ኢንቨስትመንት መዳረሻ ሆናለች።

ታድያ እንዲህ ያለ ታላቅ ስም ያላት፤ ገናና፡ የምታኮራ አገር እያለችን እንድትተራመስና እንድትታመስ መፍቀዳችን በታሪክ ዘንድ አያስወቅሰንም? በታሪክ ተወቃሾች የሚሆኑ የሕብረተሰባችን ክፍሎች የመንግሥት ባለሥልጣናት፡ ምሁራን፡ልሂቃን እና የሃይማኖት መሪዎች ናቸው። ሐቁን እንናገር ከተባለ ግን ሰላምና እርጋታ በኢትዮጵያ እንድያንሰራራ ከፍተኛ ጥረት

ያደረጉት የሃይማኖት አባቶች ናቸው፤ በዚሁ ረገድ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ካውንስል ተቋም ከፍተኛ ሚና ስለተጫወተ ምስጋና ይገባዋል። ባለሥልጣናት ምሁራንና ልሂቃን ግን፤ በጣት የሚቆጠሩ ካልሆኑ በስተቀረ: በኢትዮጵያ ሰላም ለማስፈን ጥረት ከማድረግ ይልቅ: ጸጥታውን በማደፍረስ የተጫወቱት ሚና ይመዝናል። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ደግሞ አንዳንድ ሊሂቃን የጠባብ ብሔርተኛነት ፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም በማንገብና በማራመድ የኢትዮጵያን አንድነት እንዲንኮታኮት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ወንጀለኞች ናቸው፤ አገራቸውን ከድተው ከፀረ ኢትዮጵያ የባዕድ ኃይሎች ጋር ተሰልፈዋል። አርበኞቹ ቅድመ አያቶቻችን እንዲህ ያለ ክህደት ሲፈፀምባቸው ነበር "ኢትዮጵያ ሆይ ሞት ወይ ተላላ፤ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ" ብለው ያለቀሱት።

እኔ በበኩሌ የከሃድያኑ ሸርጉድ ቀደም ብዬ አይቼው ስለነበር የዛሬ ስድስት ዓመት "ኢትዮጵያን አትረብሿት" በሚል ርእስ ግጥም ለአንባብያን አቅርቤ ነበር። ግጥሙ: በመጠኑም ቢሆን አሁን ለገጠመን ችግር አግባቢነት ስላለው ወይም ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያንፀባርቃል የሚል እምነት ስላለኝ ላላነበቡት እንድያነቡት፤ ላነበቡት ደግሞ ደግመው እንዲፈትሹት እጋብዛቸዋለሁ:- www.africanidea.org/Do_Not_Disturb_Ethiopia.pdf ነገር ግን ኢትዮጵያ በረዥሙ ታሪኳ ለበርካታ ፈተናዎች ተጋልጣ ከበርካታ መዓት የወጣች አገር ስለሆነች፤ አሁንም ቢሆን ድዮደረስ ሲስለስ እንደተነበየው ጠላቶቿ ይቸነፉ እንደሆነ እንጂ አያቸንፏትም።

ኢትዮጵያ አትቸነፍም ማለት ግን አትነሳቀልም: አትታመምም: ግዝያዊ ምስቅልቅል አይደርስባትም ማለት አይደለም። ብዙ ችግሮች ልያጋጥሟት ይችላሉ፤ ኢጋጥሟታልም። ምናልባት ኢትዮጵያ የማያጋጥማት ነገር ቢኖር ሞት ብቻ ነው፤ እኛ ልጆቿ እንሞታለን: እናልፋለን። ኢትዮጵያ ግን ልዩ ባህርይና ታሪካዊ ኃላፊነት ስላለባት ትዘልቃለች፤ ለዚህም ነው "ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኑር" የምንለው። አገራችን ኢትዮጵያ የተሸከመችው ግዙፍ ታሪካዊ ግዳጅ በአንድ "ተንችቻለሁ እንጂ አልሞትኩም" የሚል ርእስ ያዘለ መጣጥፌ ርትዓዊ በሆነ መንገድና ዘርዘር ባለ መልኩ ጠቅሼዋለሁ፤ በዚሁ መያያዣ ይመልከቱት:- www.africanidea.org/sleepy_but_not_dead.pdf

ታሪካዊ ሐላፊነት ግን ዝም ብሎ እንደዚሁ ለአገር: ለቡድን: ለግለሰቦች: ወይም ለመንግስት ባለስልጣናት የሚተው ጉዳይ አይደለም፤ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃላፊነት ነው። ይኸንን አስመልክቶ ደግሞ የዛሬ አስራ አራት ዓመት "ለኢትዮጵያ የሚበጅ የፖለቲካ ስትራተጂ መቀየስ የሁላችን ታሪካዊ ኃላፊነት ነው" በሚል ርእስ ጽሑፍ አበርክቼ ነበር። በጥናትና ምርምር ለምትገኙ ወገኖች ሁሉ በዚሁ መያያዣ ተመልከቱት:- www.africanidea.org/doc5.pdf

አሁን ለገጠመን ችግር መፍትሔ ለማበጀት ደግሞ የሁላችን ኃላፊነት መሆኑን መዘንጋት የለብንም፤ ግዙፍና ውስብስብ ያለ ችግር ነውና የገጠመን: ግዙፍና ተመጣጣኝ መፍትሔ ማቅረብ ይኖርብናል፤ አለዛ አገራችንን ወደ ከፋ መበታተን እናስገባና በዓለም ዙርያ መሳቅያ መሳለቅያ እንሆናለን። ለዚህም ነው አበው "እንረስ ካላችሁ ተስማምተን እንረስ፤ አይሆንም ካላችሁ ግን ተዉት ዳባ ይልበስ" ያሉት፤ ምርጫው የኛ ነው፤ ወይ ተስማምተን እናርሳለን ወይም ደግሞ እርሻው ዳዋ እንዲለብስ እናረገዋለን። በሌላ አነጋገር: ማርቲን ሉተር ኪንግ እንዳለው ወይ "እንደ ወንድማማች አብረን እንኖራለን ወይም ደግሞ እንደ ጅሎች እንተላለቃለን"፤ ያለችን አንድ አገር አጥፍተን ወደ አስከፊ ክስተት እንገባለን ማለት ነው።

መፍትሔው ምንድነው? አሁን ኢትዮጵያ ከገባችበት የመተላለቅ ማጥ ውስጥ እንዴት መውጣት ትችላለች? መፍትሄዎቹ ከሞላ ጎደል፤ ለመንደርደርያ ያህል የሚከተሉት ናቸው ብዬ አስባለሁ:-

፩) የኢትዮጵያ የሃይማኖት ካውንስል ተቋም: ሽማግሌዎች እና የኢትዮጵያ ሴቶች የሰላም እንቅስቃሴ አሁን የያዙትን መልካም የሰላም ተልዕኮና አላማ በጦፈ መልኩ መቀጠል አለባቸው።

፪) በዶ/ር አብይ የሚመራውን መንግሥት ተቀዳሚ ሐላፊነቱን በመወጣት፡ ማለትም የፌደራል ፖሊስና የመከላከያ ሠራዊት በየኬላውና በየመንደሩ በማሰማራት ‘ኢትዮጵያን የሚረብሿት’ ኃይሎች መንጥሮ ማውጣት አለበት። መንግሥቱ ይኸንን ግዳጅ በሚተገብርበት ወቅት ግን ሽልኮው የገቡ ወዳጅ መሳይ ጠላት ሊኖሩ ስለሚችሉና እድሉን ተጠቅመው መፈንቅለ መንግሥት ማድረግ ስለሚችሉ ከውዲሁ እንደ ቆቅ ነገሮችን ማሰላሰል ያስፈልጋል።

፫) መንግሥት ሰላምና እርጋታ ባገሪቷ እንዲሰፍን ከማድረጉም ባሻገር፡ የተጀመሩትን ትላልቅ የልማት ተቋማትና እቅዶች መሰናከል ሳይገጥማቸው መቀጠል አለባቸው፤ መንግሥት የተዘጉትን አውራ ጎዳናዎችን፡ ኃይል ተጠቅሞም ቢሆን፡ መክፈት አለበት። መንገዶቹ ከተዘጉ ወዲህ ገበሬው ምርቱን ወደ ገበያ ማቅረብ አልቻለም፤ ነጋዴው በንግድ መሰማራት አልቻለም፤ ሕዝቡም ባጠቃላይ በየጎጡ እንዲታሰር ሆኗል። አሁን ያለው የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ከዚሁ አውራ ጎዳናዎች መቆራረጥ ጋር  የተቆራኘ ነው። የአንድ ሰው ደም ሥር ከተዘጋ ሕይወት አይኖረውም፤ የአንድ አገር የመሠረተ ልማት ተቋማት ከተዘጉ ደግሞ ኢኮኖሚው (የምጣኔ ሃብት አውታሮች) ይንኮታኮታል።

፬) ጠቅላይ ሚኒስትሩና የሚንስትሮች ምክር ቤት የሰፊው ሕዝብ አመኔታ ያገኙ ዘንድ በይፋና በግልጽ ሰላምና እርጋታ እንደሚያመጡ እና የህዝቡና ያገሪቷን አንድነት እንደሚጠብቁ ለሕዝቡ በተደጋጋሚ መግለጫ መስጠት አለባቸው።

፭) መንግሥት ብቻውን ያገር ጉዳይ መሸከምና መወጣት ስለማይችል ተራማጅ ምሁራንና ሞያተኞች ምልአተ ሕዝቡን በተደራጁ የውይይት መድረኮች አማካኝነት ማስተማርና መቀስቀስ፤ በተጨማሪም አንድነቱን እንዲጠብቅ ማድረግ አለባቸው። በዚሁ ረገድ ዩኒቨርሲቲዎችና የብዙሃን መገናኛዎች የምሁራኑ ጅምር ስኬታማ ይሆን ዘንድ ማስተጋባት አለባቸው።

፮) እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ፡ ማለትም ከዛላምበሳ እስከ ሞያሌ፤ ከመተከል እስከ ጅቡቲ ጠረፍ፤ ከመተማ እስከ ሱማሌ (በርበራ) ጠረፍ ያለውን ሕዝብ የጎጥ፡ የጎሳና የክልል አመለካከትን ለግዜውም ቢሆን ትቶ የጋራ ማንነቱን የሆነውን ኢትዮጵያውነትን ማንሰራራትና ማንገብ አለበት።

፯) ድር ብያብር አንበሳን ያስር ነውና የኢትዮጵያ ሕዝብ ክንዱን በማስተባበር ሁከት ፈጣሪዎቹን ማሳደድ አለበት። በየክልሉ ካሉት የጸጥታ ኃይሎች ጋር በመተባበር ራሱን መጠበቅ አለበት፤ የጎሳ ግጭቶችን ዳግመኛ እንዳያገረሹ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለበት።

፰) ወጣት ኢትዮጵያውያን ልዩ ታሪካዊ ግዳጅ እንዳለባቸው መገንዘብ አለባቸው፤ የወጣቱ ልዩ ግዳጅ ከመሪነት መረካከብ ጋር የተቆራኘ ነው። ወጣቱ ትውልድ የነገይቱ ኢትዮጵያ መሪ ስለሆነ ከወዲሁ የሰላም አርበኛ ሆኖ ኢትዮጵያውነቱን ማጠናከር አለበት። በነገራችን ላይ ይህ ፅሑፍ ወደ ህትመት ከመሄዱ በፊት በወጣቱ ዘንድ ተስፋ የሚሰጡ ጅምሮች ተከናውነዋል፡- ሀ) የኢሕአዲግ ወጣት ሊግ አባላት በመቐለ ተሰብስበው ስለ የጋራ የኢትዮጵያ አጀንዳ ተወያይተዋል፤ ለ) በደቡብ ክልል የኢትዮጵያ ወጣቶች የሰላም ጉባዔ ሰላምን እንዴት ማስፈን እንደሚቻል ተወያይተዋል።

፱) ባሁኑ ግዜ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በአንድነት ኢትዮጵያ ሃገራቸውን ከኋላ ቀሪነት፤ ከድህነትና ከድንቁርና ነፃ አውጥተው ባፋጣኝ መንገድ አገራቸው በልፅጋ፡ መጥቃ እና ለምታ፤ የተዋሃደች ጠንካራ አገር ሆና በዓለም አቀፍ ገበያ ተፎካካሪ እንድትሆን፤ በአፍሪቃ ደረጃ ደግሞ የአህጉሩ መሪ እንድትሆን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

፲) ከላይ የተጠቀሱትን ርእሰ ነገሮችና ቁምነገር አዘል ትንታኔዎች በግብር እንዲተረጎሙ ታድያ በምሁራን ኢትዮጵያውያን የሚመራና በመንግሥት የሚደገፍ የሃገራዊ እርቅ ጉባኤ መካሄድ አለበት። በዚሁ ረገድ እኔ በበኩሌ ለማበርከት ቃል እገባለሁ፤ ለመንደርደርያ ያህል ደግሞ ከዚህ

ቀደም ያበረከትኩት National Reconciliation and National Development ይኸውና፡- www.africanidea.org/national_Reconcillation.html

የሃገራዊ እርቅ ዋና ዓላማ “ተስማምቶ ማረስ” ነው፤ “ዳዋ ይልበስ” የሚለወን የተስፋ መቍረጥና የሽንፈት መንፈስ ገና ለገና ያስወግደዋል፤ ምክንያቱም ያገር ጉዳይ የእልህ ፖለቲካ እና የግል ጥቅም ማደራጃ ሳይሆን ከፍተኛ የጋራ ኃላፊነት የሚጠይቅ ሆኖ በስምምነትና በፈቃደኛነት የተመሠረተና ዘላቂነት ያለው ፡ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያሻግር አጀንዳ ስኬታማ በሆነ መንገድ ለመተግበር የሚቀይስ ስልት ነው፤ አብሮ እንደ ወንድማማች እና እህትማማች በፍቅር ለመኖር እንጂ እንደ ጅሎች እርስ በርስ መተላለቅና አገርን ማጥፋት አይደለም። ስለሆነም ሁሉም ኢትዮጵያዊ በዚሁ አገጣሚ አንድነትህን አጠንክር፤ ልዩነቶችህን አስወግድ ወይም በወል እደር ወደ ጎን አስቀምጠው፤ በብሔርነትህ ጥላቻን የስነልቦናህ አካል እንዲሆን ከማድረግ ይልቅ ኢትዮጵያውነትህ በአእምሮህ ፀንሰህ፡ በልብህም አስተውለህ የበግ ለምድ የለበሱትን ተኵላዎችን ከጉያህ ተወሽቀው አንድነትህን እንዳይሸረሽሩት በጥሞና ተከታተላቸው፡ ከቻልክም አጋልጣቸው፤ ራስህን አድን፡ አገርህንም አድን።

**መልካም ዕድል ለኢትዮጵያ**

የደራሲውና የአፍሪቃ ልማትና ትምህርት ተቋም (አልትተ) መብት በሕግ የተጠበቀ ነው። ታሕሳስ ፪፮ ፪፻፩፩ All Rights Reserved. Copyright © Ghelawdewos Araia and the Institute of Development and Education for Africa (IDEA) 2019